# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

ነሐሴ ፲፮ እሑድ ሲውል

የቃሉ ትርጉሜ ስርወ ቃሉ ከርመ፣ ከረመ ካለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጓሜውም ወርኃ ዝናም፣ ወርኃ ነጐድጓድ፣ ዘመነ ባሕር፣ ዘመነ አፍላግ፣ ዘመነ ጠል፣ ዘመነ ደመና፣ ዘመነ መብረቅ ማለት ነው። የክረምት ዘመን ከሰኔ ፳፮ እስከ መስከረም ፳፭ ቀን ድረስ ነው።

## የዕለቱ ምስባክ

ቀደሰ ማኅደሮ ልዑል
እግዚአብሔር ውስተ ማዕከላ ኢትትሀወክ
ወይረድአ እግዚአብሔር ፍጽመ

ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ
እግዚአብሄር በመካከሏ ነው አትታወክም
እግዚአብሔር ፈጽሞ ይረዳታል።

መዝ ፵፭፥፭

ወንጌል፥ ማቴ ፳፮፥፳፮-፴፩
ቅዳሴ፥ ዘእግዚእነ (የጌታችን)

## የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

«እሕትነ ይብልዋ»

### በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ሮሜ ፰፥፴፩-ፍጻሜ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ፪ኛ ዮሐ ፩፥፩-ፍጻሜ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፩፥፲፪-፲፭ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

## የዕለቱ ትምህርት

# ዕረፍተ ድንግል ማርያም

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እንደ ኢትዮጵያ ቀን አቆጣጠር ጥር ፳፩ አንድ ቀን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ያረፈችበት «በሥጋ የሞተችበት» ዕለት የሚታሰብበት ቀን ነው። ነሐሴ ፲፮ ቀን ደግሞ የእመቤታችን ትንሣኤ እና እርገቷ ታስቦ የሚውልበት ቀን ነው። ነሐሴ ፲፮ ቀን በየዓመቱ በየአብያተ ክርስቲያናቱ ተሰብስበን ስብሐተ እግዚአብሔር ለማድረስ፣ የወንጌሉን ቃል ለመስማትና የንስሐ ትምህርት ለማግኘት ምክንያት የሆነን ይኸው የድንግል ማርያም የእረፍትዋ የትንሣኤዋ የእርገቷ መታሰቢያ ነው።

ድንግል ማርያም የእግዚአብሔር ወዳጅ ከሆኑ ቅዱስ ኢያቄምና ቅድስት ሐና ከተባሉ ወላጆችዋ ተወልዳለች። የድንግል ማርያም ወላጆች መካኖች ነበሩ፤ ልጅም አልነበራቸውም። ነገር ግን እግዚአብሔር ፈቃዱ ከሆነ ብለው ልጅን እንዲሰጣቸው ሳያቋርጡ ከመጸለይ በቀር በመምከናቸው እግዚአብሔርን አያማርሩም ነበር። እነዚህ የተባረኩ ሰዎች በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደዱ ስለነበሩ ኢያቄም ከሸመገለ ቅድስት ሐናም የመውለጃ ጊዜዋ ካለፈ በኋላ በተኣምር ድንግል ማርያምን ወለዱ። ይህም እንደ ዮሐንስ መጥምቅ ወላጆች እንደ ዘካርያስና እንደ ቅድስት ኤልሳቤጥ፤ እንደ አብርሃምና እንደ ሣራ ማለት ነው (ዘፍ ፲፰፥፩-፲፮ ። ሉቃስ ፩፥፰-፳፮)።

የድንግል ማርያም ወላጆች ድንግል ማርያምን ለእግዚአብሔር ለመስጠት ተስለውና ቃል ገብተው ስለነበር በተወለደች በሦስት ዓመትዋ ወደ ቤተ መቅደስ ወስደው አስረከቡ። ይህም ደግሞ እንደ ነቢየ እስራኤል እንደ ሳሙኤል ወላጆች ማለት ነው (፩ኛ ሳሙ ፩፥፲፩-ፍጻሜ)።

እመቤታችን በቅድስና በድንግልና በንጽሕና የታደለች ስለነበረች የአዳም ተስፋ፣ የሞት መድኃኒት፣ የዘለዓለም ሕይወት አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን ሰው ሆኖ ከእርሷ መወለድን ፈቀደ። እርሱ ሰማይና ምድር የማይችሉት መለኮታዊ አምላክ ነው። ነገር ግን የሚሳነው ነገር ባለመኖሩ ከድንግል ማርያም ያለ ወንድ ዘር በተኣምር ተወለደ። ድንግል ማርያምም «ወላዲተ አምላክ» ለመባል በቅታለች።

### ትንቢት እና የድንግል ማርያም መዋዕለ እድሜ

ስምዖን አረጋዊ የተባለ ጻድቅ ሰው የጌታን መወለድ ሳያይ እንዳይሞት ዘወትር ጸሎቱ የነበረ ሰው ነው። እግዚአብሔር ጸሎቱን ተቀብሎት ከእድሜ ላይ እድሜ እየተጨመረለት የቆየ የእድሜ ባለ ጸጋ ሲሆን ይህ ሰው ጌታ በተወለደ በአርባ ቀኑ በቤተ መቅደስ ከእናቱ ጋር አግኝቶት የልቡ ደረሰለት። እንደነበረውም ሥርዓት ጌታን ታቅፎ አንተን አይቻለሁና ከዚህ ዓለም አሰናብተኝ ከማለት ጋር እመቤታችንን በተመለከተ ትንቢት ተናግሮ ነበር (ሉቃስ ፪፥፳፭)። ትንቢቱም እንዲህ ይላል፥ «ስምዖንም ባረካቸው እናቱን ማርያምንም እነሆ የብዙዎች ልብ ሃሳብ ይገለጥ ዘንድ ይህ በእስራኤል ላሉት ለብዙዎቹ ለመውደቃቸውና ለመነሳታቸው ለሚቃወሙትም ምልክት ተሹሟል። በአንቺም ደግሞ በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል (ሉቃ ፪፥፴፭)። በዚህ የትንቢት ቃል ውስጥ እመቤታችንን «በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል» ሲል በዘመንሽ ሁሉ እንደ ሰይፍ የሚቆርጥ ሃዘንና መከራ ይደርስባሻል ማለቱ ነው። ምክንያቱም ከእርሷ የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ

# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

## ዕረፍተ ድንግል ማርያም …

ነሐሴ ፲፮ እሑድ ሲውል

ዓለሙን የሚያድነው በመከራውና በመስቀሉ እንደነበር በመንፈስ ስለተገለጠለትና ድንግል ማርያምም በሄሮዶስ ቁጣ ከግብጽ ስደት ጀምሮ እስከ ቀራንዮ ድረስ በልጅዋ የተነሳ የሚደርስባትን መከራ መንፈስ ቅዱስ ስላመለከተው ነው። በእርግጥም ድንግል ማርያም በጌታ የተነሳ የደረሳበት ሃዘን እንደ ሰይፍ የሚቆርጥ ነበር። በተለይም ጌታ የማዳን ሥራውን ለመፈጸም የጀርባ ሥጋው አልቆ አጥንቱ በረዶ እስኪመስል ድረስ ሲገረፍ፣ እጆቹ እግሮቹ በችንካር ሲበሳሱ፣ ጎኑ በጦር ሲወጋ፣ በመስቀል ሲሰቀል፣ ደሙ እንደ ውኃ ሲጎርፍ፣ ከስቃዩ የተነሳ ተጠማሁ ሲል፣ በውኃ ፈንታ መራራ ሃሞት ሲሰጠው አንዲት እናት ይህንን ሁሉ ግፍ በሚፈጸምበት ልጅዋ አጠገብ ሆና ይህንን ሁሉ መከራ ማየት እንደሰይፍ የሚቆርጥ ሃዘን ከመሆኑም በላይ በአእምሮ ተቀርጾ እስከ ምንጊዜውም የማይጠፋ ከሕይወት ጋር የሚጣበቅ የመከራ ሙጫ ነው። በድንግል ማርያም ይህ ሁሉ ደርሶባታል፤ በተለይም የእስርዋ ታሪክ መጻህፍት እንደሚናገሩት በቀራንዮ ከዮሐንስ ጋር ያየችው የልጅዋ መከራ እስከ ጊዜ ሞቷ አስለቅሶአታል። ለዚህ ነው ጌታ በማዳን ጉዞው ወቅት በደረሰበት መከራ ድንግል ማርያም የመከራው ተሳታፊ ናት የሚባለው። ስለዚህ እመቤታችን ድንግል ማርያም የተሰጣትን የመከራና የሃዘን ዘመን ፈጽማ ፈተናውን ሁሉ በትዕግስት አልፋ በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ጥር ፳፩ ቀን አረፈች።

### ጌቴሰማኒ

ሐዋርያት በድናን ሊቀብሩ ወደ ጌቴሰማኒ ይዘዋት ሲሄዱ አይሁድ እንደልማዳቸው በምቀኝነት ተነሳስተው ልጅዋ እንደተነሳ ትነሳለች ብለው በድናን ቀምተው በእሳት ለማቃጠል በኃይል ወደ ሐዋርያት ሲገሰግሱ ሐዋርያት ተበታተኑ። ከአይሁድ ወገንም አንድ ደፋር በድናን እወስዳለሁ ብሎ ሲሞክር መልአከ እግዚአብሔር እጁን ቆርጦ ጥሎታል። በዚህ ጊዜም መላእክት የእመቤታችንን አስከሬን ወስደው በገነት አኑረውታል። ሐዋርያትም በስምንተኛው ወር በነሐሴ አስከሬንዋን እንደገና ከጌታ ተቀብለው በጸሎትን በምህላ ቀብረውታል። በዚህ የቀብር ሥነ ሥርዓት ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ቶማስ አልነበረም።

በተቀበረች በሦስተኛው ቀን እንደ ልጅዋ ትንሣኤ ተነስታ ስታርግ ቶማስ ሀገረ ስብከቱ በደመና ተጭኖ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጣ ያገኛታል። በዚህ ጊዜ ሌሎች ሐዋርያት ትንሣኤዋን አይተው ለእርሱ የቀረበት «ፈቀደ ይደቅ እምደመናሁ» ይላል። በፊት የልጅሽን ትንሣኤ ሳላይ ቀረሁ፤ አሁን ደግሞ የአንቺን ሳላይ መቅረቴ በማለት ከደመናው ሊወረወር ቃጣው። በዚህ ጊዜ እመቤታችን ቶማስን አጽናናችው፤ ከእርሱ በቀር ትንሣኤዋን ሌላ እንዳላየ ነገረችው፤ ለምስክር እንዲሆነውም ሰበናዋን ሰጥታው አረገች። ቶማስ ከሐዋርያት ጋር ኢየሩሳሌም በተገናኙ ጊዜ «እመቤታችንን እኮ ቀበርናት» ብለው ነገሩት። እርሱም አውቆ ምስጢሩን ደብቆ «አይደረግም - ሞት በጥር በነሐሴ መቃብር» አለ። ለማሳየትም መቃብር ሲከፍቱ አስከሬኗ አልነበረም። በዚህ ጊዜ እርሱ እመቤታችን ተነስታ አርጋለች ብሎ ሁኔታውን ተረከላቸው። ለምስክርም ይሁንህ ብላ የሰጠችውን ሰበንዋንም አሳየችው፤ ሰበንዋን ለበረከት ቆራርጠው ተካፍለው ወደየአገረ ስብከታቸው ተበታትነዋል። በዓመቱ ትንሣኤሽን ቶማስ አይቶ እንዴት እኛ ይቅርብን ብለው ከነሐሴ አንድ ጀምረው ሱባዔ ገብተዋል። ጌታም የሚሳነው ነገር ባለመኖሩ ወዳጆቹን ለማስደሰት በነሐሴ አሥራ አራት ቀን ትኩስ በድን አድርጎ አምጥቶ ሰጥቶአቸው ከቀበሯት በኋላ በነሐሴ አሥራ ስድስት ተነስታለች። በሙሉ ታሪኩን በውዳሴ ማርያም ትርጉም መመልከት ይቻላል።

### ከዚህ ታሪክ ውስጥ የሚገኘው ትምህርት

፩) ውጤቱ መልካም ይሁን እንጂ በክርስቶስ የተነሳ የሚያጋጥመው ፈተና ከባድ መሆኑን ነው። ድንግል ማርያም በክርስቶስ ምክንያት የደረሰባት ሃዘን ከክብደቱ አንጻር በሰይፍ እስከመመሰል ደርሶልና (ሉቃ ፪፥፴፭)።

፪) በመዝሙር ፴፫፥፯ «የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል ያድናቸውማል» የሚለው አምላካዊ ቃል በተግባር ሲፈጸም መታየቱ ነው። ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ቅዱሳን መናቅና መደፋፈር ልማዳቸው ከሆኑ አይሁድ መካከል የእመቤታችንን በድንዋን ከሐዋርያት ቀምተው ለማቃጠል ሲሞክሩ ቅዱሳን መላእክት ፈጥነው ተቃዋሚዎችን በተለመደ ኃይላቸው ቀጥተውና አስደንግጠው የእመቤታችንን በድን ነጥቀው በመውሰድ በክብር በገነት አስቀምጠዋልና።

፫) በማቴዎስ ፯፥፯ «ለምኑ ይሰጣችኋል ፈልጉ ታገኙማላችሁ መዝጊያ አንኳኩ ይከፈትላችሁማል» የሚለው አምላካዊ ቃል ከምን ጊዜውም በበለጠ በሥራ መገለጹን መገንዘብ ነው። እንዴት ለሚል ሰው፥
ሀ) ሐዋርያት የእመቤታችንን አስከሬን በጌቴሰማኒ ለመቅበር በጸሎት ፈጣሪያቸውን ለምነው ተሰጥቶአቸው በጌቴሰማኒ ቀብረዋታልና፤
ለ) ትንሣኤዋን ቶማስ አይቶ እነርሱ ባለማየታቸው እንደገና ለማየት ፈልገው በሱባዔ ከልብ ጌታን በጸሎት በመጠየቃቸው የልባቸውን አድርሶላቸዋልና፤
ሐ) በክርስቲያናዊ ሕይወት የፈተና ብዛት የድል ምልክት መሆኑን ያሳያል። ለምን? ድንግል ማርያም በሰይፍ በተመሰለ ፈተና ካለፈች በኋላ ድልን ተጐናጽፋለችና።

ክርስቲያኖች ሆይ፥ እኛም የቅዱሳንን ታሪክ መተረክ ብቻ ሳይሆን እንደ ቅዱሳን በፈተና የጸናን ለመሆን እንዘጋጅ። «በፈተና የሚጸና የተባረከ ነው» ይላልና (ያዕ ፩፥፲፪)

ወስብሐት ለእግዚአብሔር … አሜን።

ትምህርት በአባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህ ፲፱፻፹፯ ዓ.ም.